# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የአፍሪካ የ2021 ምርጥ ማዕከላዊ ባንክ ተብሎ ተሸለመ

- የባንኩ ገዥ ዶክተር ይናገር ደሴ ምርጥ ገዥ ተብለው ተመረጡ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የአፍሪካ የ2021 ምርጥ ማዕከላዊ ባንክ ተብሎ **ካፒታል ፋይናንስ ኢንተርናሽናል** (*cfi*) በተባለ ዓለምአቀፍ ድርጅት ተሸለመ፡፡

ባንኩ ተሸላሚ ሊሆን የቻለው በማዕከላዊ ባንክ ገቨርናንስ/አመራር ረገድ በመላ አፍሪካ ከሚገኙ ባንኮች መካከል ብልጫ ያለው ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገቨርናንስን በተመለከተ ስትራትጂያዊ ግቡንና ዓላማውን ለማሳካት ይቻለው ዘንድ ለባለሙያዎቹ የአቅም ግንባታም ሆነ ሌሎች ማበረታቻዎችን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ይህም ባለሙያዎችን ለመሳብና ያሉትንም ለማቆየት፤ ብሎም የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ አስችሎታል፡፡

በአገሪቱ የፋይናንስ ዘርፍ የተመዘገበው ከፍተኛ ዕመርታ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያካሄዳቸው የሪፎርም ሥራዎችና ያስገኙት ውጤቶች በመሆኑ ባንኩን ተሸላሚ አድርገውታል፡፡

ባንኩ ለዚህ ሁሉ ውጤት የበቃው ደግሞ ዶክተር ይናገር ደሴ ወደ ባንኩ ገዥነት በመጡ ባለፉት ሦስት ዓመታት ዉስጥ መሆኑን ነው ካፒታል ፋይናንስ ኢንተርናሽናል የተባለው ዓለምአቀፍ ድርጅት ያስታወቀው፡፡

ድርጅቱ "A Man for All Season and All Reason: NBE Governor Takes Bank to the Forefront" ሲል ነው ዶክተር ይናገርን የገለጻቸው፡፡

ዶክተር ይናገር ወደ ባንኩ ገዥነት ከመጡ ጀምሮ በተወሰዱት ርምጃዎች የአገሪቱ የፋይናንስ ሴክተር ላይ በጉልህ የሚታይ ዕድገት መምጣቱን የመሰከረው ድርጅቱ፣ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ማክሮኢኮኖሚ እንዲረጋጋና እንዲያድግ እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል በብስለት መምራታቸውን ድርጅቱ አስረድቷል፡፡

ምንም እንኳን የውስጥም ሆነ የውጭ ጫናዎች ቢኖሩም የአገሪቱ ኢኮኖሚ በዕድገት ጎዳናውሊቀጥል የቻለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተጫወተው ትል¡ሚና መሆኑን አመልክቷል፡፡

የዓለማችን ትልቅ ተግዳሮት በሆነው በኮቪድ 19 ወረርሺኝ ወቅት እንኳን የፋይናንስ ሴክተሩ እያደገ የመጣው በዶክተር ይናገር የሚመራው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከቁልፍ አጋሮቹ ጋር በመተባበር ባደረገው የቅርብ ክትትልና አመራር መሆኑን አመልክቷል፡፡

ከመስከረም 2013 ዓ.ም አንስቶ የተካሄደው የገንዘብ ቅየራ በስኬት መጠናቀቁ ደግሞ የአገሪቱ ባንኮች የፋይናንስ ተደራሽነታቸው እንዲጎለብትና ገንዘብ በሚገባ ማሰባሰብ እንዲችሉ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማድረጉንም ድርጅቱ አብራርቷል፡፡

ምን ጭ፦ - https://cfi.co/menu/corporate/2021/06/national-bank-of-ethiopia-nbe-putting-the-central-bank-at-the-true-centre-of-economic-revival/

https://cfi.co/menu/corporate/2021/06/yinager-dessie-nbe-governor-takes-bank-to-the-forefront/